# አጽማቸው የፈለሰው የመላከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ የአምስቱ ዘመን ተጋድሎ

**ቀሲስ አስተርአየ**
**(nigatuasteraye@gmail.com) ነሐሴ ሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓ.ም**

*የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውን እንመሰክራለን (ዮሐ 3፡11)*

ዓለም እንደሚያውቀው የጣሊያን ጦር በአድዋ ጦርነት እጅግ በሚያሳፍር ቅጣት ተቀጥቶ ከኢትዮጵያ ምድር መውጣት ለመላ አውሮጳ የሐፍረት ማቅ መከናነብ ምክንያት ሆነው።

በዚህ ታሪካዊ ውርደት የተሸማቀቀው ጣሊያን፤ ዘመናዊ የምድርና የሰማይ ጦሩን ከበፊቱ በላቀ ሁኔታ አደራጅቶ፣ኢትዮጵያን በጎሳ ሸንሽኖ በቋንቋ ለያይቶ እርስ በርሱ የማዋጋት ስልቱን ቀምሮ፣ አማራና ተዋህዶ ቤተክርስትያንን የማጥፋት እቅዱን ዘርግቶ እንደገና በ1928 ዓ.ም. ወረረን፡

የመጀመሪያውን የክተት ጥሪ የሰሙ ኢትዮጵያውያን የየራሳቸውን መሳሪያ እየገዙና ሥንቃቸውን እያዘጋጁ ከሸዋ፣ ከወሎ፣ ከምስራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከመካከለኛውና ደቡቡ ክፍል ወረራውን ለመመከት በማይጨው በኩል ዘመቱ። በተከዜ በኩል ከጎጃም ከቤገምድርና ስሜን ጣልያን መሰረቱን ወደ ጣለበት ወደ ትግሬ ዘመቱ። በወረራ በተያዙት ቦታዎች የነበሩ ከህድያን ካህናትም ባንዳወችን በመደገፍ ወረራውን በሽብሽባ እያጀቡ የጣሊያንን መንግስት አጸደቁ።

ዘማቾች አርበኞቻችን እንደ ምንይሽር፣ በልጅግ፣ ጓንዴ፣ ጦርና ጎራዴ በመሳሰሉ ዘመናዊ ባልሆኑ መሳሪያዎች በባንዳዎች እየተመራ በሰማይ መርዝ በምድር ባሩድ እሚረጨውን የጣሊያን ጦር ገጠሙ። ከእንዲህ ዓይነት የወረራ ተጋድሎ በኋላ ትግሬ የዘመተቱት አርበኞቻችን ወደ መሐል፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለስልት ሲያሸገሽጉ የኢትዮጵያ ጦር ተፈታ፤ ንጉሡም ከአገር ወጡ፤ ጣልያንም በባንዳዎች እየተመራ አገሪቱን እያዳረሰ ነው የሚል ወሬ በብቸና ተሰማ።



ወሬው እንደ ዛሬው በቴክኖሎጅ የሚጣራ ስላልነበረና ከብቸናና አካባቢዋ ቀደም ብለው ትግሬ የዘመቱት አርበኞች ተመልሰው ስላልመጡ በሕዝቡ ዘንድ ውዥንበር ተፈጠረ። ይህ የውዥንብር ወቅትም ፈሪውንና ደፋሩን፤ ወላዋዩንና ቆራጡን ለመለየት ታላቅ ጥበብና ዘዴ የጠየቀበት ወቅት ሆነ። ይኽንን ውዥንብር ያስተዋሉት ሊቀጠበብት አድማሱ ጀንበሬ የሰፈር ዋዘኞች፣ ቀልደኞች፣ ሰነፎችና አውደልዳዮች በቀላሉ በፍርፋሪ ተደልለው ለጠላት መሳሪያ በመሆን አገር እንደሚጎዱ ተገነዘቡና ሕዝብን ማስጠንቀቅ ጀመሩ።

<u>መሰሎኒ አገራችንን ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊቀጠበብት አድማሱና ሌሎች የበቁ ካህናት እንደ በላይ ዘለቀ ላሉ ተናዳፊ አርበኛ ተዋጊዎች ድል ምሰሶ፣ ወጋግራ፣ ግድግዳና ማገር በመሆን ያበረከቱትን የአርበኝነት ተጋድሎ ጀመሩት።</u>

በዚህ ወቅት ሊቀጠበብት አድማሱ ሰሎሞን **ይኀይይ ረሚዕ እንዘ አልቦ ዘይዴግኖ ወጻድቅሰ ከመ አንበሳ ውኩል¡** እያለ በተግሳጹ 4፥1 የተናገረውን እየጠቀሱ፤ የብርብራ ቅጠል እንደተነሰነሰበት እንደ ባህር አሳ መሸበር አይኖርብንም፤ በእምነት፣ በመንፈስ፣ በሥነ-ምግባርና በአካል ጸንተን እንቁም! እጠቃለሁ ብሎ እንደማያስብ ያንበሳ ደቦል በሙሉ ልብ እንነሳ እያሉ "በአገርና በሚስት የለም ዋዛ" የሚለውን ብሂል መመሪያው አድርጎ ከሚኖረው ያካባቢው ሕዝብ ጋር መመካከር ጀመሩ።

ሊቀጠበብት አድማሱ ጀንበሬ የጠና እምነታቸውንና ስነ ባህርያቸውን የቀረጹበትን ቅኔ፣ አእምሯቸውን ያሰፉበትን የመጽሐፍ ትርጓሜና እግዚአብሔር ያደላቸውን ብሩህ አዕምሮ ተጠቅመው፤ <u>ንትናጸር</u> በሚል መዋቅር የደብሩን ሊቃውንት ማደራጀትና ማነቃነቅ ጀመሩ።

*ንትናጸር* የሚለውን ሐሳብ የወሰዱት የመጀመሪያውን አቡን አባ ሰላማን ወደ ኢትዮጵያ የላከው ቅዱስ አትናትዮስ ከተናገረው ነው። ሙሉ ሀሳቡም እንደሚከተለው ነው።

**ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚ ብሩሀት።ተናጸሩ በበይናቲክሙ አሐዱ ምስለ ካልዑ። ሕቱ እምውስቴትክሙ በአበይዎ ኢ.ይቁም ወኢ.ይህበር ምስሌክሙ በጸልዮ ኢ.ዘማዊ ወኢ.ቀታሊ ኢ.ሰራቂ ኢ.ሀሳዊ . . . . ገስጽዎ ዝልፍዎ በግህድ ለእመ ቦቱ አበሳ ዘለሞት፤(ቅ አ 8)**

ወደ አማርኛ ሲመለስ "እናንት ካህናት የእግዚአብሔር ዓይኖችና ብሩሃን መሆናችሁን አትዘንጉ። በመካከላችሁ በውሸታምነት፣ በሌብነት ፣ በነፍሰ ገዳይነት፣ በዋዘኛነት፣ ባስመሳይነት፣ በጥቅም አሳዳጅነት፣ በዋልጌነትና ባመንዝራነት የሚከሰስ፣ የሚወቀስና የሚታማ ካህንና ቄስ እንዳይበክላችሁ እርስ በርሳችሁ ተፈታተሹ" የሚል ነው፡፡

ሊቀጠበብት አድማሱ ካህናትን ሰብስበው ከላይ የተገለጡት አስነዋሪ ባህርያት ያሏቸውን ካህናት፤ በጓደኝነት፣ በዝምድና፣ በጉርብትና፣ በግል ጥቅም፣ በፍርሃትና በይሉኝታ ሳትታሰሩ ገስጹ። ከከንቱ ባህሪያት ተላቀው ለእምነታቸው፣ ለቤተክርስትያናቸው፣ ላገራቸውና ለሕዝባቸው እንዲቆሙ ምከሩ፡፡ በዚህ መንገድ ዋልጌ ካህናትን መክረን ታልመለስን ወይም እንደ አረም ነቅለን ታልጣልን የእግዚአብሔር ረድኤት ይርቀናል። ሕዝብም በእኛ ላይ እምነት አይጥልም፤ የምናስተምረውንም ሆነ የምንነግረውን አይሰማም፡፡" ሲሉ አስጠነቀቁ፡፡

ማስጠንቀቂያው ሰርጸ የገባቸው ካህናትም ምክራቸውን ተቀብለው ዋዘኞችን፣ ቀልደኞችንና ዋልጌዎችን አስተምረውና መክረው በጠንካራ እምነትና መንፈስ እንዲጠኑ አደረጉ፡፡ በጽኑ እምነትና መንፈስ የቆሙ ካህናት ራሳቸውን ካደራጁ በኋላ ሕዝቡን ማደራጀት ጀመሩ፡፡ እያንዳዱ ቄስ በየማህበር ቤቱ፣ ሰንበቴ ቤቱና የንስሀ ልጆቹ ቤት እየሄደ ስለ ጣልያን አረመኔነት፣ ስለ ፋሽሽት አገርና ሃይማኖት አጥፊነት እንዲያስተምር አደረጉ፡፡

አገርንና ሃይማኖትን በሚያጠፋ በፋሽሽት መወረራችንን በእናርጅ እናውጋ፣ ሞጣ፣ ጉንደወይንና በሌሎችም ገዳማት ለሚኖሩት

መነኩሳት፤ በየመቃር ቤቶችና ዋሻዎች ዘግተው ለሚኖሩ ባህታውያን እንዲዳረስ አድርጉ። መነኮሳት ከየገዳማቱ፤ ባህታውያንና ከዘጉቸው ከየዋሻዎቻቸውና መቃብር ቤቶቻቸው ወጥተው ሕዝቡን በማንቃት እንዲሳተፉ አደረጉ።

ሊቀጠበብት አድማሱ ሕዝቡን የሚያደራጁ ካህናት ከብቸና ደብር ጀምረው በእነቆራ፣በለምጨንና በደንሳ፣በግራርማ፣በሸረር፣ በየምጥች፣ በየዱሀ ስላሴ ገዳም፣በጎፍጭማ፣ከዓባይ አፋፍ እስከሚገኘው እስከ ከጎይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰበካ፤ የነቁ ካህናት ያልነቁትን ካህናትና ያልሰማውን ሕዝብ እያነቁና እያደራጁ የተጋድሎ ቅስቀሳ የሚደርጉ የታመኑትን ካህናት አሰራጩ።

<u>በላይ ዘለቀ ወንድሙን እጅጉ ዘለቀን አጎቶቹን ተሰማ ላቀውን አወቀ ላቀውን እንየወ ላቀውን አስከትሎ በዙሪያ በተሰባሰበው ፋኖ ታጅቦ ከሶማ በመገስገስ አባይ አፋፍ ላይ ካለው ጎይ ጊዮርጊስ ላይ ዘልቆ ብቅ አለ።</u> (በነገራችን ላይ የተሰማ ላቀው ታናናሽ ወንድሞች እንየውና አወቀ ወንድማቸውን ተሰማ ላቀውን ተከትለው የወጡ ልጆች ነበሩ) የየጎይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካህናት ባካባቢው ከሚኖረው ህዝብ ጋራ እያሸበሸቡ ተቀበሉት። ይህን ያቀባበል ትንግርት የተሳተፉ እኔ ለትምህርት ካካባቢው እስክርቅ በጎይ ይኖሩ የነበሩ እነ ባለህ ረዴ፤ በኋላ ካምቦ ላይ የጠጅ ቤት የነበራት እህቱ ሞኘነት ረዴና የነሱ ትንሽ ወንድም ጎትረሌ ይኖር የነበረው ብዙአለ ረዴ ይተርኩት ነበር።

<u>እንደ ብረት የመይታጠፈው የበላይ ጀግንነት፤ እንደ እሳት በመንቀልቀል ላይ ያለው የነሊቀጠበብት አድማሱ የእምነት የሞራል ጽናት እንደ እሳትና ብረት በጎይ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተወሀደ።</u>

በሊቀጠበብት አድማሱ የተጫረው የካህናትና የሕዝብ ሰንሰለታዊ እንቅስቃሴ በበላይ ዘለቀ መሪነት ሶማ ላይ ተሰብስቦ ለነበረው ፋኖ ታሪካዊ የድል በር ከፈተለት። ባጭር ጊዜ ውስጥ ከሶማ ጀምሮ በብቸና አውራጃ ሕዝባዊ ማዕበል ተንቀሳቀሰ።

ሊቀጠበብት ባሰለጠኗቸው የካህናት ዘማቾችና በሚከበሩ አዛውንቶች የነቃው ወጣትና ጎልማሳ፦

*ካባይ ከፊላው ዳር የሚያገሳው ኮርማ*

*ምድሩን አናወጠው  በለምጨን ተሰማ፦*

 *የሚለው ግጥም እያቅራራና እንደ ግስላ እየፎከረ በሚያስገርም ወኔ እየተሽቀዳደመ በበላይ ዘለቀ የሚመራውን የፋኖዎች ጦር ተቀላቀለ።*

*ልጃገረዶችና እናቶች በወንዶች ጀግንነት ተደስተውና በወኔ ተሞልተው በነሊቀጠበብት አድማሱ የተዘጋጁት የቅኔ መምህራንና ተማሪዎች እንዲያንጎራጉሩ የሰጧቸውን፦ ኢትዮጵያን ወክለው*

*የእጅጉ ዘለቀ የነበላይ ነኝ*

*በርግጎ የሚሸሽ ፈሪም አይነካኝ*  *እያሉ በበላይ ዙሪያ ያለውን የፋኖ ጀግንነት ወኔ  የሚያሞካሹ ፈሪውን እየነቀፉ ደፋሩን እያወደሱና እየደገፉ በማንጎራጎር ፤ወገባቸውን ሰንገው ለፋኖዎች ስንቅ እያዘጋጁ ለማቅረብ ተሽቀዳደሙ።።*

*ሌሎች ካህናት ሕዝቡን የማንቃትና የማደራጀት ተግባር በእነማይ፣ በደባይ ጥላት ግን፣ በሸበል፣ በጉብያ፣ በደጀን፣ በውድሚት፣ በባሶሊበን፣ በጎዛምንና በሌሎችም ሥፍራዎች እንቅስቃሴውን አስፋፉ። በካህናትና በታዋቂ የማህበረሰቡ አባላት የነቃው ሕዝብም የጎበዝ አለቆችን በየአካባቢው እየመረጠ ለፍልሚያ ተዘጋጀ።*

*በጎበዝ አለቆች መካከል የመሪነቱን ቦታ ለመያዝ ባህላዊ ፉክክር መኖሩ አልቀረም። ከፉክክሮች አንዱ የሸበል በረታን ጦር በሚመራው በበላይ ዘለቀና፤  የሸበል ኲታገጠም የሆነውን የጉባያ ምክትል ወረዳን ጦር ይመራ በነበረው አርበኛ ጫኔ ተረፈ (በኋላ ፍታራሪ) መካከል የተከሰተው ፉክክር ነበር።*

*ጫኔ ተረፈ የምትመካበት ቦራ ባዬ የሚባል የጦር አዝማች ነበራት። የበላይ ዘለቀ የጦር አዝማቹ ደግሞ ወንድሙ እጅጉ ዘለቀ ነው። በወቅቱ ጫኔ ተረፈም በሸበል በጉባያ በብዙ ፋኖወች የተከበበች እንደ በላይ ዘለቀ ስመ ጥር ነበርችና  የጠቅላላው ጦር መሪ መሆን ፈለገች።*

*"አንተ ለኔ ናልኝ እጅጉን ለቦራ*

*እንደ አንጋች አዳሙ ላስግጥህ አሞራ"* የሚል ፈታኝ መልእክት ለበላይ ዘለቀ ላከችበት። ጫኔ በቆፍጣናነቱ አንቺ እየተባለ ይጠራ የነበረ ጀግና ነበርና ከጫኔ የፈለቀው ውድድር ፈታኝነቱ ህዝብ የሚከፍል ፈተና ለበላይ ብቻ አልነበረም። እነሊቀ ጠበብትን ሁሉ የሚፈት ነበር።

በብቸና አውራጃ እንዲህ ዓይነት የጀግንነት ፉክክር ሲከሰት ካህናትና የተከበሩ ያገር ሽማግሌዎች ጣልቃ በመግባት አስታርቀው የእርስ በርስ ፉክክሩ ለእርስ በርስ መጎዳኛ ሳይሆን ለመጠነካከርና ላካካባቢ አጥርና መከታ እንዲሆን ያደርጉ ነበር። ይህን ባህላዊ የወንድነት ውድድር፤ በተከበሩ ካህናትና ያገር ሽማግሎች ባህላዊ እርቅ ተፈጸመ። በኋላም በምክትል ወረዳዎች ያሉ የጎበዝ አለቆች በበላይ ዘለቀ የጦር አዛዥነት ተጠቃለው እንዲመሩ አስማሟቸው።

በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ የጎበዝ አለቆች በበላይ ዘለቀ የጦር አዛዥነት ሊዋጉ ቢስማሙም ሊቀጠበብት አድማሱ ከሚመሩት የካህናት አርበኞች ሰራዊት አፍንግጠው በባንዳነት የቆሙ ደፍተራ ታየ የሚመሩ ጥቂት ደፍተሮችና መነኮሳት ተከሰቱ።

በከሀዲው ደፍተራ ታየ የሚመራው የባንዳ ቡድን "ጣሊያን ገባ እየተባለ እሚወራው ውሸት ነው" እያለ ጣሊያን ለማታለል ይጠቀምበት የነበረውን ዘዴ በመንዛት ሕዝቡን ማዘናጋት ጀመረ። ይህን የማዘናጋት ውንብድናውን የሰማው በላይ ዘለቀ፤ አይኑን ተነብር እንደ ተጣላ አንበሳ አጉረጥርጦ "ይህንን እያዋዛህ የምታሰራጨውን ማፍዘዣ ማደንዘዣ ስብከት አቁም¡ ብሎ መሪውን ደፍተራ ታየን መጀመርያ መከረው። ምክሩን አልቀበል ሲልም አርባ ገርፎ ለቀቀው። ገርፎ እንደ ለቀቀውም ባንዳው ታየ እጅግ ከሚያከብራቸው ሊቀጠበብት አድማሱ ዘንድ በላይ ዘለቀን ከሰሰው።

በላይ ዘለቀ በደፍተራ ታየ ተከሶ የቀረበላቸው ሊቀጠበብት አድማሱም "ለፌዘኛ፣ ለአውደልዳይ፣ ለሞላጋና ለሾክሿካ ፍርድና ብትር ይገባዋል!" ሲል ሰሎሞንም ፈርዷል ብለው ምሳሌ 19፡ 29 እንደ ማስረጃ አቀረቡለት። ቀጥለውም "ዘያነብብ ጽሩአ ያገብኡ ሎቱ ቃለ በእለተ ደይን (ማቴ 12፡ 36) ይህን በመሰለ እለተ ደይን ዋዛና ፈዛዛን ለሚጫወት ሰው ቅጣት ይገባዋል ያለውን የክርስቶስን ቃል አልሰማህም?" ሲሉ

አፈጠጡበት። በመጨረሻም "የበላይ ፍርድ ይግባኝ የሌለው ክርስቶሳዊና ሰለሞናዊ ፍርድ ነው። የሚበጅህ ራስህን በሁለት እጆችህ ይዘህ እኔን ያየህ ተቀጣ! እያልክ ለሚመስሉህ ሞላጋዎችና አውደልዳዮች ማስተማር ነው" ብለው አሰናበቱት። ሊቀጠበብት ወስላቶችን በእንዲህ ዓይነት ተግሳፅና ቅጣት እየመለሱ፣የባንዳው ቁጥር አመነመኑት፡፡

በሊቀጠበብት አድማሱ የሚመራው የሊቃውንቱ ቡድን ጣሊያንን በደረቀ ግንድ፤ ባንዳውን በገለባ፣ በላይ ዘለቀንና አርበኞቹን በእሳት እየመሰሉ ካህናትንና ሕዝቡን ማስተማሩን ቀጠሉ፡፡ "ደረቅ ግንድ እሳት ሲነካው ይነዳል፤ ይከስላል፤ ገለባ በእሳት ፊት አይቆምም በወላፈኑ ይሸመቀቃል፤ ይኮሳተራል። እነ በላይ ፊት የጣሊያንና የባንዳዎች ሀይል ገለባ ነው፤ የነበላይ እሳትነት ያሸማቅቀዋል፤ ይኮስትረዋል፣ ይለበልበዋል፣ አመድ ያደርገዋል!" እያሉ ሕዝቡ በሚገባው ቋንቋ ሰበኩ፡፡ <u>ለበላይ ዘለቀ ኮስትር የሚለውን የፈረስ ሥም ሰጥተው **አባ ኮስትር በላይ** ብለው ማስጠራት ጀመሩ፡፡ ያካባቢው ሕዝብም የበላይን ጀግንነት ለመግለጽ **የኮስትር አሽከር** እያለ እንዲፎክር አደረገ።</u>

ሜዳው፣ጫካውና ገደሉ ባርበኞች ሲሞላ፤ ቀበሌው በቀረርቶ፣ በፉከራና በዋሽንት ዜማ ሲናወጥ፤ ቤቶችና ጎጆዎች ልጃገረዶችና እናቶች በሚያብስሉት ያርበኞች ስንቅ ማብሰያ ጪስ ሲታጠኑ፤ <u>የአየሩ መዓዛ ጀግና ጀግና ሲያውድ በፈሪነት፣ በሞላጋነት፣ በቀልደኛነት፣ በፌዘኛነትና በዋልጌነት ይታወቁ የነበሩ ካህናት ተሸማቀቁ።</u> ካገልግሎትም ራሳቸውን አገለሉ። ሊቀጠበብት አድማሱም ራሳቸውን ያገለሉትን ዋልጌ ካህናት አድንቀው "የምትገለሉት ከማቁረቡና ከማጥመቁ እንጅ ከስህተታችሁ ከተርማችሁ ህዝቡን የምታገለግሉባቸው ሰፊ ዘርፎች አሉ¡ ብለው ግራ ጌታ፤ ቀኝ ጌታ፤ መጨኔና ሙሉ ጌታ በመሳሰሉት ያገልግሎት ዘርፎች አሰለፏቸው።

በብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር <u>**ንትናጽር**</u> በሚል ሥርዓት ያዋቀሩትን የአርበኛ ካህናት የተጋድሎ መዋቅር ¡<u>**ኢንህድግ**</u> በሚል መዋቅር አስፍተው ፊደል ቆጥረው ወደ አደጉበት ዲማ ቅዱስ ጊርጊስ ገዳም ሄዱና በዚያ አካባቢ ያሉትን ሰበካዎች ማደራጀትና ማንቀሳቀስ

ጀመሩ። በደብረ ወርቅ፣ በሞጣ፣ በየረዝና፣ በየዘረዘር፣ ያለውን ህዝብ በገድ እና በሌሎች ጫካወች እየተሰባሰቡ እንዲወያዩ ምክር ሰጡ።

የተደራጁት ካህናት በየዱህ ግራ መስመር ላይ ያሉትን አንስላላ ኪዳነ ምህረት፣ ጋታንስ ገብርኤል፣ ሥር ኢየሱስ፣ ዘብች ኢየሱስ፣ ድቢሳ ማርያም፣ ደቤት ማርያም ያሉትን ታላላቅ ደብሮችንና እንደዚሁም በጉባያ፣ በደጀን፣ በአዋባል፣ በባሶ ሊበን፣ በደረቤና በሌሎችም ታላላቅ አድባራት ያሉት ያብነት ጉባእያት መምህራን ጉባያቸውን እያጠፉ እንቅስቃሴውን በመቀላቀል ህዝቡን አጠናከሩ። የቅኔ መምህራኑ

ወዲያ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ተጣራ፤ ወዲህ ማዶ ሆኖ ሌላ ሰው ወይ አለው፤
ኅበዝ ተጠንቀቁ ይህ ነገር ለኛ ነው¡ የሚለውንና መሳሰሉትን ግጥሞች እያዘጋጁ በየጎጡ በየኮረብተው በየደብሩ የሚኖረው ህዝብ እርስ በርሱ እተጠራራ በላይን እንዲደግፍ አደረጉ።

ጣሊያን ጥቂት ባንዳወችን በመጠቀም ደጀንን አቋርጦ የቀፊት አቦ ላይ ጣቢያውን ቆረቆረ። የቀፊት አቦ አካባቢ ያሉትን እነከርከርን፣ የቀጋንንና ጎትረሌን ምሽግ አደረገ። ባህታዊ የሚያስመስል ጉኒና መንኩሴ የሚያስመስል የሰሌን ቆብ የደፉ ቀጣፊዎች ሞላጋወች እምነት ያልነበራቸው ሞራለ ቢሶች መዋጋት የፈሩና፤ ግማሹችም ጣሊያንን ለማገልገል የተሰለፉ ከሀዲዎች፤ ጣሊያን የሚባል የለም። ጠላት መጣ እያሉ ወሬ የሚነዙት ፖለቲከኞች ናቸው፤ ጣሊያን ገባ የሚል ወሬ ቢኖርም እንኳ ትግሬ ውስጥ ነው። ተከዜን ተሻግሮ በጌምድር አልገባም። በነ ሊቀጠበብት አድማሱ ወሬ ተታላችሁ አትግደል የሚለውን የፈጣሪን ቃል ሽራችሁ ሰው ለመግደል መሳሪያ ለመግዛትም ንብረታችሁን አትሽጡ። አርፋችሁ ርሻችሁን እረሱ፤ አትዋጉ ዝምብላችሁ ጸልዩ ሱባዔ ግቡ እያሉ ፈጥኖ ለመረዳት የሚዘገየውን ያካባቢውን ህዝብ ግራ የሚያጋቡ አዘናጊዎች ለነሊቀጠበብት አድማሱ ትልቅ ፈተና ሆኑባቸው።

ሊቀጠበብት አድማሱም የመጀመሪያው መነኩሴ አባ እንጦንስ ነው። እናንት መነኩሴዎች እንደምሳሌ ልትጠቅሱት የሚገባችሁም እንጦንስ ነው። እንጦንስ ደጋግሞ የተሰለፈው ከተወረረው ከተዘመተበት

ህዝብ ጋር ነው። ንስሀ ግባ ተመለስ አትዋጋ ያለውም ወራሪውን ነው። እናንተም እንደ እንጦስ ከተወረረው ከተበደለውና ከተዘመተበት ጎን በመሰለፍ እያበረታታችሁ ወራሪውን ጣሊያንን ስሀ እንዲገባ ወዳአገሩ እንዲመለስ ማድረግ ሲገባችሁ፤ ወገናችሁም ወራሪውን ነቅቶና በርትቶ እንዲከላከል ማበረታቱን ትታችሁ፤ ይህን የመሰለ ታሪክ የማይረሳው ደባ በህዝብና በአገር መስራታችሁ ኢትአብስ ለሰብአ ሀገርከ ወኢታስህት ርእሰከ በማእከለ ህዝብከ፡ (ሲራ 7፡7 የሚለውን የመጽሀፉን ቃል አሳብላችኋል። ለአገር ለወገን ለሚመጣው ትውልድ እንድንጠነቀቅ የሚያዝዘንን ቃል ረስታችሁ በሰመይና በምድር ስርየት የሌለው ኃጢአት ፈጸማችሁ።

ጠላት ባህር ተሻግሮ ወሮን እያለ፤ አትከላከሉ ንስሀ ግቡ ሱባዔ ግቡና ቁጭ ብላችሁ ጸልዩ ማለት፤ እሳት እየነደደባችሁ ሳትንቀሳቀሱ ቁጭ ብላችሁ ነዳችሁ ለማለቅ ጸልዩ ማለት ነው። ይህም አምላክ የሰጠንን የመከላከል የተፈጥሮ እውቀትና አቅም አዘናግታችሁ፤ የተሰጠንን ጸጋና የሰጠንን አምላክ ማስካድ ነው። በመወረር ላይ ያለ ህዝብ እጅግሩን አጣጥፎ ቁጭ ብሎ ራሱን እየከሰሰ እየወቀሰ እንዲኖር ለማድርገና ይህንንም ለልጆቹ እንዲያወርስ ማድረግ ተፈጥሯችንና ፈጣሪያችንን መፈታተን ነው።

እኛ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነት ካህናት፤ ኢትዮጵያ አገራችን ወደፊተና በገባችበት በዚህ ወቅት ሱባዔ ገብተን ቁጭ ብለን ወደፊተና አታግባን ብለን አንጸልይም። ህዝባችንንም ንስሀ ግባ ወደፊተና አታግባን እያልክም ጸልይ ብለን አንነግረውም። ከገባንበት ፈተና እንዲያወጣን ረድዔቱን እየተማጸን ከቦታ ቦታና ከደብር ደብር እየተንቀሳቀስን ጀግኖችን የማበረታት የጀግኖችን ሚስቶችና ልጆች የማጽናናት ሐላፊነት እንዳለብን የክርስትና መጻህፍቶች ይነግሩናል ካሉ በኋላ እናንተ ግን የጠላት መሳሪያወች ናችሁ። ብለው የጎበዝ አለቆች የፋኖወች መናህሪያ ወደነበረው ገድ ወደሚባለው ቦታ ተወስደው እንዲቆዩ አደረጓቸው።

ጠላት መጣ እያሉ ወሬ የሚነዙት ፖለቲከኞች ናቸው፤ ጣሊያን ገባ የሚል ወሬ ቢኖርም እንኳ ትግሬ ውስጥ ነው። ተከዜን ተሻግሮ

በጌምድር አልገባም። ቄሱ ዝም ብሎ እንዳይቀድስ ከመቅደሱ እንዲወጣ፤ መነኮሳቱ ባህታውያኑ በየዋሻቸው በየመቃብር ቤታቸው ዘግተው እንዳይጸልዩ፤ መነፍቃን በሆኑ በነ ሊቀጠበብት አድማሱ ወሬ ተታላችሁ፤ አትግደል የሚለውን የፈጣሪን ቃል ሽራችሁ ሰው ለመግደል  መሳሪያ ለመግዛትም ንብረታችሁን አትሽጡ።  አርፋችሁ ርሻችሁን እረሱ፤ አትዋጉ ዝምብላችሁ ጸልዩ ሱባዔ ግቡ አገር አማን ነው እያሉ የሰበኩትን የሚጠይቅ እና ህዝቡም እንዲነጋገርበት ለማድረግ፦

አገር አማን ነውይ? በእርግጥ አማን ነውይ?
ሰርተን መኖራችን ጤና ላይሆን ነወይ?

የሚለውን አነጋገሪ እና አጠያያቂ ቀስቃሽ ግጥም እያዘጋጁ ጎልማሳው ወጣቱ በየአፋፉ ላይ እየቆመ እያንጎራጎረ እንዲያቅራራበት እንዲሸልልበት አደረጉ።

ጣሊያን ቅራርቶውን ለማፈን እንቅስቃሴውን ለመግታት ንብረት መዝረፍና ቤቱን ማቃጠል በተለይ የበላይ ደጋፊ ነው ብሎ በሚጠረጥረው ቤተ ሰብ ላይ ያረመኔ ተግባራቸውን የበለጠ አከፉት።

ይህንን ግፍ ለመመከት፤ ለመግታትታና ለመጨረሻም ለማቆም፤ የነበላይ ዘለቀን ያርበኝነት መንፈስ የበለጠ የሚያጎላምስ የሚያቀጠጣልና የሚተኩስ፤ ለአርበኛው ጥበብ የሚለግስ ምክር  በሊቀጠበብት አድማሱ የሚመራው የሊቃውንት ቡድን በሚቀጥለው በቅዱስ ዮሐንስ ተግሳጽ የተመሰረተ ትምህርት ማስተማራቸውን ቀጠሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውንም   ወለእመ አውአዩ ቤተነ በእሳት ወበርበሩነ ኢንአምር፤ ወዓዲ ንህነኒ ንገብር ዘንተ በርእስነ እምቅድመ ይግበር ብነ ካልዕ፤ ወናቀስል ነፍሰነ በኩሉ እለት (ድ ዘ ቅ ዮ 24; 23-25)  የሚለው ነው።

ይህም ማለት፦ ጣሊያንና ባንዳዎቹ ቤቶቻችንን አቃጠሉ፤ ንብረታችንን ዘረፉ፤ እህቶቻችንን ደፈሩ ብላችሁ አጻፋ ለመመለስ እንደነሱ አረመኔ አትሁኑ። ቤቶቻቸውን ስታቃጥሉ ንብረታቸውን ስትዘርፉ፤ የነሱን ቤተሰቦች አትጉዱ። ሚስቶቻቸውን አትድፈሩ

ከጣሊያን ጋራ ቢወግኑም ቀሪ ዘመዶቻችን መሆናቸውን አትርሱ ። እነሱ የፈጸሙትን ሁሉ ክፉ ተግባር እንፈጽም ብንል፤ ወናቆስል ነፍሰነ በኩሉ እለት እንዳለው ዮሀንስ አፈወርቅ በጣሊያን ሴቶች በጣሊያን ልጆችና ቤት አይደለም። በነሱ ምክር ተታለው ይህንን  አሰቃቂ ግፍ የፈጸሙብን የራሳችን ወገኖች መሆናቸውን አዘንጋ፤ አጻፋ ለመመለስ በምታደርጉት ነገር ሁሉ ተጠንቀቁ፤  ምንም የማያውቁትን ቢያውቁም ምንም ማድረግ በማይችሉት ሚስቶቻቸው ልጆቻቸው ላይ ጉዳት ማድረስ ራስን ማቁሰል ነው። ህይወታቸውን በማይጎዳ ይልቁንም በሚያስተምር መንገድ አጻፋውን መልሱ እያሉ አስተማሩ።

የነሊቀጠበብት አድማሱን ሚዛናዊ መርሆ እየሰሙ ፋኖዎች ቢታገሱም በጣልያን ድጎማ የሚተዳደሩ ባንዶች ግን የሕዝብን ንብረት ከመዝረፍና ቤት ከማቃጠል አልተቆጠቡም ።

እነ ሊቀጠበብት አድማሱ ዑቅ ወተዐቀብ በሕቅ እስመ ምስለ ቀታሊከ ተሀውር። ኩሉ እንስሳ ያፈቅር ዘመዶ ወኩሉ ሰብ ያፈቅር ቢጾ። ወኩሉ ነፍስ ይትጋባእ ምስለ ዘከማሁ ወሰብእ ምስለ ዘይዛወጎ። በዓይቴ ይትአረክ ተኩላ ምስለ በግዕ ከማሁ ኃጥእ ምስለ ጻድቅ   (ሲራ 13፥ 13__17)" የሚለውን እየጠቀሱ ማስተማራቸውን አጠናከሩ።

ይህም ማለት፦ ካራጅህ ከጠላትህ ከጣሊያን ጋራ ተባብረህ ጣሊያን የሚጥልልህን ፉርኖ እየበላህ በአንጋችነትና በነገር አቀባይነት የምታገለግል ሁሉ ተጠንቀቅ ! ተሰማርተህ ያለውኽ አራጁን እንደማያውቅ እንስሳ ካራጅህ ጋር ነው። ከወገኑ ራሱን ቆርጦ ከሮማውያን ጋራ የሚያወዳጅ ከአውሬ የከፋ ፍጡር እንጅ እንደሰው አንቆጥረውም።  እያሉ አስተማሩ።

ሁሉት ልብና ሁለት ምላስህ አዝላችሁ፤ በላይንና ጣሊያንን አስተባብረን ከሁለቱም ሳንጋጭ የበላይን ለጣሊያን የጣሊያንን ለበላይ በማመላለስ ይህን ዘመን እናሳልፋለን ብላችሁ የምታስቡ ሰዎች ራሳችሁን ከወጥመድ እንዳትከቱ ተጠንቀቁ ! እያሉ የሰሎሞንን ተግሳጽ ዘይሰርእ በቅድመ አርከ መስገርተ ይወድዮን ለአእጋረ ዚአሁ ተግሳጽ 5፡5 የሚለውን መሰረት በማድረግ አስጠነቀቁ። ይህም ማለት፦ ተጠልፎ

*የሚወድቅበትን ወጥመድ ለወገኑ የሚያዘጋጅ ሰው፤ ባዘጋጀው ወጥመድ የራሱ እግር መታሰር ይገበዋል።*

*መነኩሴ ባህታዊ እየመሰሉ ለወገን አዛኝ ተቆርቋሪ ወዳጅ እየመሰሉ በተሰበኩት ወገኖች ላይ የጥርጥር ስሜት የተከሰከሰባቸውን አዘናጊ መንፈስ ከህሊናቸው ለማጠብ፤ በመከስከስ ላይ ያሉትንም እየገሰጹ ለማሸማቀቅ፦*

*ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው*
*አስቀድሞ መምታት አሾክሻኪውን ነው።*

*የሚልና የመሳሰሉ ግጥሞችን ህዝባዊ ዜማ በማልበስ ለሚያቅራሩትና ለሚፎክሩት ጎልማሶች እያቀበሉ የሕዝቡን መንፈስ ቀሰቀሱ።*

*ባንዳ ሲያዩ ፊታቸው እንደ አንበሳ የሚቆጣው፣ ጸጉራቸው እንደ ነበር የሚቆመውና ዓይናቸው እንደ ክረምት ኩሬ የሚደፈርሰው በላይ ዘለቀና አርበኞቹም የነሊቀ ጠበብትን ስነ ልቡናዊ የወንድ በር ከፋች መርሆ በመጠቀም፤ በአድርባይነትና በፍርሃት ልቡ የተከፈለበትን በመጠገን፣ ያፈነገጠውን በመመለስ፣ አልመለስም ብሎ ለጠላት ያደረውን ቤቱን በማቃጠልና ንብረቱን በመውረስ ከጣሊያን እጅ እየፈለቀቁ ከራሳቸው ጎን አሰለፉት። <u>በዚህ ፈታኝ ወቅት ወገኑ እየሞተ፤ እርሱ እንደ አሳማ እየበላ የሚተኛ፤ ለሆዱ ሲል ለጣልያን የሚሰግድ ሆዳምና ጆሮ ጠቢ ሾክሿካ ካካባቢው ጥርግ ብሎ ጠፋ።</u> ነገር አመላላሽና ሾክሿካ ባንዳ ሲጠፉ ወጣቱ፣ ጎልማሳው፣ ሽማግሌው፣ ባልቴቱ፣ ሴት ወንዱ በሲቃ በጣልያን ላይ ያገኘውን ድንጋይና ጠጠር መወርወሩን የተለመደ ተግባሩ አደረገው።*

*ለጣልያን የሚሰግድ ሆዳምና ጆሮ ጠቢ ሾክሿካ ከካባቢው እንዲጠፋ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ባለቅኔዎች ቅዱስ ያዕቆብ የተናገረውን ገጽ ንባብ መሰረት አድርገው፤ አ ሆ በልዎ ለዘለቀ ልጅ፤ ወእንቢየ በልዎ ለግራዝያን ጋኔን፤ የሚል ቅኔ እየተቀኙ፤ ለበላይ ዘለቀ ሆታ፤ ለ ግራዚያኒ እምቢታ በወጣቱ ልብ እንዲቀረጽ አደረጉ። ግራዝያንን በሰይጣን በላይን በክርስቶስ መስለው እየተቀኙ ሕዝቡ በግርማ በሞገስና በድፍረት በየደብሩ በየአደባባዩ በላይን ተከትሎ እንዲተም አደረጉ።*

ባገር ከሀዲዎች አማካይነት እየተመራ ጣልያን የተማረኩበትን ለማስለቀቅ እነ ሊቀጠበብት ባልጠረጠሩበት ቀንና ሰርጎ ወደ በረንታ ዘልቆ ያገኛቸውን በየዱሁ አካባቢ ሕዝብን እየቀሰቀሱ የሚያደራጁ አርበኛ ካህናትን በነጭ ገደል አፋፍ ላይ ደርድሮ በመደዳ ረሽኖ ሬሳቸውን ወደገደሉ ወረወረው። በዚህ አሰቃቂ ግድያ በርካታ ሊቃውንት ካህናት ሰማእታት ሆኑ።

ከጭፍጨፋው ያመለጡ ካህናትና አርበኞች በመቃ 2፡19 የተፃፈውን አስታውሰው፤ መሳሪያ ሆነው ይህን ግፍ ላስፈጸሙ ከሀድያን ካህናት ዘላለማዊ ጸጸት እንዲሆናቸው፤ እንደናንተ ለሀገር ጥፋት መሳሪያ ሆነን የራስን ወገን ከማስገደል ያገርንም ጥፋት ከማየት እናንት የጨፈጨፋችኋቸው ይሻላሉ ለማለት፦

> ሥጋየን ይብሉና ደሜን ይጠጡት
> የሀገሬን ጥፋት ቆሜ ከማያት¡

የመሳሰሉትንን ዜማዎች ህብረተሰቡ እንዲያንጎራጉር አደረጉ። የካህናቱን መጨፍጨፍ የሰማው የበላይ ዘለቀ ጦር ቁጣ እንደ እሳተ ገሞራ ገነፈለ። እንደ እሳተ ገሞራ በገነፈለው ቁጣና እንደ ችቦ በተንቦገቦገው ቁጣ የነደደው ጦር በለምጨን በኩል ዘልቆ ዋስዳን፣ የቀጋንን፣ ጎትረሌን እያስተባበረ ጣሊያን የቀፈት አቦ ላይ ካምቦ ብሎ የመሰረተውን ምሽግ እንደ በሰበሰ አጥር ሙሉ በሙሉ ደርምሶ የፋሽሽትን ሰራዊት በመደዳ ደምስሶ ሬሳቸውን እንደ ምንጣፍ ዘረጋው።

ብዙ ጣሊያኖችና ተላላኪ ባንዶችን ከነጦር መሳሪያቸው ማረከ። በዚህ ድል አያሌ የመሰሎኒ ሰራዊትና ባንዳ ሞርኮኞችን የፍጥኝ ታስረው ያዩ ካህናት የጌታችንን የኢየሱስ እናት ድንግል ቅድስት ማርያም፤ የተዋረዱትን ከፍ አደረጋቸው፤ ትእቢተኞችን አዋረዳቸው " ብላ የተናገረቸውን በጸሎት መልክ አደረሱ።

በተለይ ወገናቸውን ከድተው ከጣሊያኖቻ ጋር በተማረኩት ባንዳዎች በጣም አዝነው ኢትአብስ ለሰብአ ሀገርከ ወኢታስህት ርእሰከ በማእከለ ህዝብከ¡ (ሲራ 7፡7) የሚለውን እየጠቀሱ ጣልያን እንደ ውሻ የሚወረውርላችሁ ፍርፋሪ ጣፍጧችሁ ወገናችሁን የከዳችሁና ያስጠቃችሁ

ማፈሪያዎች በፍርኖና ከጣሊያን በምታገኙት ተብለጭላጭ ነገር ወጣቱን ከማሳሳት ተገለሉ" ሲሉ ባንዶችን አስጠነቀቁ።

አርበኞ ካህናት፤ ማርያም፦ አዕበዮሙ ለትሁታን ወፈነዎሙ ራቆሙ ለብኡላን ፡ ብላ የተናገራቸውን ርእስ በማድረግ ፍካሬ ማርያም ብለው ሰይመው ለአርበኞች ነገሩ። ይህንን ትምህርት የተቀበለው በላይ ዘለቀም ፍካሬ ማርያምን ያርበኝነት መርህ አርጎ ይጠቀምበት ነበር።

በዚህም ምክንያት በላይ በማርያም ምሎ የገባውን ቃል ሳይፈጽም ምራቁን አይውጥም ነበር። በላይ ለማርያም ያለውን ክብር የሚያውቅ አንድ አስመሳይ አባ ኪዶ የሚባል መነኩሴ በበላይ እጅ ድንገት ብትወድቁ በማርያም ካላችሁት ስቃይ አያበዛባችሁም ብሎ ለጣሊያኖችና ባንዶች አካፈላቸው ። ጣሊያኖችና ባንዶች በበላይ እጅ ወደቁና፤ እንደተነገራቸው "በማርያም ይዘንኻልና ስቃይ አታብዛብን" እያሉ ይማፀኑት ጀመር።

ከበላይ ጋር የነበሩት እነ ሊቀጠበብት አድማሱ፦ የሰው አገር ውረሩ የምትል ማርያም አናውቅም፤ እናንተ የምትጠሯት ማርያም የመሶሎኒ እንጅ የክርስቶስ እናት አይደለችም! እኛ ኢትዮጵያውያን የምናውቃት የኢየሱስ እናት ኪዳነ ምህረት የነጻነት ሰባኪ ናት። ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስም፦ ቅዱስ ቄርሎስ ይትቃረኖ ለሰይጣን ዘሞአነ ቀዳሚ ወተጻብአ በእንቲአነ ወገደፎ መትህተ ወአዕረቆ እምኀይሉ ወበእንተዝ ግብር መጽዓ በሥጋ ዋህድ ቅዱስ ያርእየነ ከመ ንህነ ተሳተፍነ ፍጻሜሁ፤ ሃ ም 79፡25። ብሎ የገለጸው ነው ብለው ተናገሩ።

ይህም ማለት፦ሰብሮ ገብቶ ያሸነፈንን ሰይጣን ስለኛ እንደኛ ሆኖ ሰይጣንን ተፋለመው። አምዘግዝጎ ጣለው ከክብሩ አዋረደው ስለዚህም በሥጋ ራሱን ገለጸ እኛንም የድሉ ተሳታፊወች አደረገን። በላይ ይህን የክርስቶስን ተግባር እየፈጸመ ነው ብለው አብራሩት።

## የበረሀው ዳኛ የጫካው ንጉሥ

በላይ ሰው አይፈራም ያለ ክርስቶስ።

ተልከፍካፊ ውሻ ሰብሮ  ገብ ሰላቶ

ተመቻችቶ አይኖርም በጦቢያ ውስጥ ገብቶ  የሚለው ግጥም ተደረሰና ወንዱ በሆታ ጨፈረበት። ሴቱ በልልት እስክስት አወረደበት።

አዋቂወችን ያለፈውን በበላይ ዘለቀና በነ ሊቀጠበብት አድማሱ ጀንበሬ መካከል የነበረው የመንፈስ የህሊና ህበረትና መከባበር የነበራቸውን መደማመጥ በትዝታ ሲያነሱት እጅግ ይደነቃሉ።

ስለተማረኩት ጣሊያኖችና ባንዳዎች የነበራቸው አያያዝ እጅግ ይገርማቸዋል።

እመ ርህበ ጸላኢከ አብልኦ ወእመ ጸምአ አስትዮ ዘንተ እመ ገበርከ አፍህመ እሳት ታስተጋብእ ዲበ ርእሱ። ወእግዚአብሔር የዓስየከ ሠናያተ፡ ተግሳጽ （1፡21__22）። የሚለውን የሰሎሞንን ምክር እየጠቀሱ፤ ጣሊያን በእጃችሁ ቢወድቅ ሊጎዳችሁ ካልተንቀሳቀሰ በቀር አትደብድቡት፤ አትግደሉት።

ይልቁንም እንዳይርበው፣ እንዳይጠማውና ተጠንቀቁለት። እንደ እግዚአብሔር እንግዳ አርጋችሁ አክብራችሁ ካስተናገዳችሁ በኋላ ወደ መጣበት ሸኙት።  ይህን ማድረግ በሁለት መንገድ ይጠቅማል። የድል ባለቤት አምላክ አሸናፊነትን ድልን ከጠበቀው በላይ ያበዛል። ተማርኮ የተለቀቀው ጠላት  ደግ ከሆነ ከኛ ጎን ተሰልፎ ይዋጋል። ባይወጋም የሚዋጋንን ይቃወማል" እያሉ ያስተምሩ ነበር። አርበኞቹም ምክራቸውን ሰምተው የጣሊያኖችን ሰብአዊ መብታቸውን እየጠበቁ ዓባይ በርሃ አካባቢ አቆይተው ለቀቋቸው፤ ባንዶችን ግን ደረቅ ባቄላ ተንበርክከው እንዲፈጩ አደረጓቸው።፡

የበላይ ዘለቀ ጦር በሊቀጠበብ አድማሱ ጀንበሬና በሌሎችም ካህናት በዚህ መንገድ  እየታገዘ፤  እንደ ህይሉ በለው፣ መንገሻ ጀምበሬ፣ ነጋሽ በዛብህና ሌሎችም በሞጣ፣ በዳሞት፣ በአቸፈር፣ በሜጫና በአገው ምድር ጣልያንን ከተፋለሙት የጎጃም ፋኖዎች የጦርይ አዛዦች ጋር እየተቀናጀ

ጣልያንን እንኳን የህንጻና መንገድ መስሪያ የድንኳን መትከያ ጌዜ አሳጥቶ፤ እመቤታችን ትእቢተኞችን በተናቸው እንዳለችው ጣሊያንና ባንዳወቹ ተበተኑ።

በዚህ ድል የተደሰቱት ካህናትም በወንፈል፣ በደቦ፣ በዓመት በዓልና በሰርግ የሚዘፈኑ ዘፈኖች፣ ቀራርቶዎችና ፉከራዎች በአባ ኮስትር በላይ ላይ እንዲያተኩሩ አደረጉ። በዚያ ዘመን በበላይ ዘለቀ ዙርያ የተደረሱት ዘፈኖች፣ ቀራርቶዎችና ፉከራዎች አባዛኞቹ የተመሰረቱት ወንድነትና ጀግንነትን በሚያጎላምሱ ፤ ፈሪነትና ባንዳነትን በሚገስጹ መንፈስ ላይ የተመሰረት ናቸው። ቀልብን ይዞ ጭልጥ በሚል ዋሽንት የሚታጀበው ሽለላና ቅረርቶ ፈሪን የሚያስንቅ፤ የተኛውን የሚያነቃ፣ የነቃውን የሚያንቀሳቅስ፣ የሚንቀሳቀሰውን ወደ ተግባር የሚገፋፋ ረቂቅ መንፈስ ነው።

የበላይን መሪነት አስፍላጊነት ለመግለጽም ዐርከ ምእመን ሥራየ ህይወት ወእለ ይፈርህዎ ለእግዚአብሔር ይረክብዎ፡ (ሲራ 6፡16) የሚለውን ይጠቅሱና እምነትና ወኔ ያለው መሪ ኮሶን እንደሚያሽር እንቆቆ ነው። ኮሶ እንደ እሚያሽር እንቆቆ ያለ መሪ እሚያገኝምም በአምላኩ ላይ እምነት ያለውና የመንፈስ ልእልናን የለበሰ ሕዝብ ነው። በላይን የመሰለ የቀውጢ ቀን የጦር መሪ ጎጃም ያፈራው የጎጃም ህዝብ እምነቱ፣ ባህሉና ወኔው እንደ ኮሶ እሚያሽር እንቆቆ ስለሆነ ነው" ብለው የምትቀጥለውን ስንኝ አፈለቁ።

ዓባይ ሲደፈርስ ሲመስል እንቆቆ
ጋሬጣው ጎጃሜ ገባ ባጭር ታጥቆ

ሊቀጠበብት አድማሱ ከብቸና ደብር እስከ ጎይ የዘረጉትን የካህናትና የህዝቡን ሰንሰለታዊ ህብረት በላይ ዘለቃ ተላብሶ ያላንዳች ጥርጥር ጣልያንን ድል ያደረገበትን የእምነቱን ጽናት በመመልከት ምሳሌ ቢያጡሉት ቃል ዘውእቱ እርአያሁ ለእግዚአብሔር ወዘረሰዮ ባህቲቱ ተትህተ ወነስአ አርያ ገብር ወአስተርአየ በሥጋ ወተጻብአ ቦቱ። ወህመ በእንቲአነ በሥጋ በአምሳለ ሥጋ ኃጢአት ከመ ይትሀፈር ኃጢአት በሥጋሁ (ሃ አ ምእ 76፡24) እያለ ቄርሎስ ስለ ክርስቶስ

የማዳን መንገድ የተናገረውን እያወሱ  ተናገሩ። ይህም ማለት፦"የአብ ልጅ ቃል የማርያም ልጅ ሆኖ። ከማርያም በነሳው ሰውነት ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ጠላት ዲያብሎስን ሊፋለመው በሰው መሆን ገባ" እግዚአብሔር በበላይ ዘለቀና በአርበኞቹ  ልብ አድሮ ዘመናዊ መሳርያ እስታፍንጫው ታጥቆ የመጣውን ፋሽሽት ጦር ተፋልሞ አሸነፈ። እያሉ አወደሱት።

አርበኞቹ የተፋለሙትና ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡትም ለግል ጥቅም ሳይሆን በየዘመናቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እንዳደረጉት ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለህዝባቸው፣ ላገራቸው፣ ለሃይማኖታቸው ለሰንደቃቸውና ክብር ነው" ሲሉ ተናገሩ።

ጣሊያን ተባሮ ጦርነቱ ሲቆም ሊቀጠበብት አድማሱ በጦርነቱ ወቅት የተረሸነውን፣ ገደል የተወረወረውን፣ ከእነ ቤቱ የተቃጠለውን፣ የቆሰለውን፣ የተሰበረውንና በመንፈስ የተጎዳውን ሕዝብ በጸሉታቸው ለማሰብ ከዲማ በታች ግርኛ ከሚባለው ቆላማ ቦታ ከደብረ ጥሞና ገዳም ለሱባኤ ገቡ።

ሊቀ ጠበበት አድማሱ የግል ተፈጥሯቸው ልዩ  ቢሆኑም ይህን ጥበብና ትእግስት ያገኙት ከዚህችው ጥንታዊት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ነው። የበላይ ዘለቀን  ጀግንነት ያስረጸውም የበረንታ የሸበል የመላው ጎጃም ባህልና ወኔ ነው። ኢትዮጵያ በተወረረችባቸው ዘማናት ሁሉ፤ ወራሪዎችን  እየተከላከለች ድንበሯን ያስጠበቀችው እኒህን በመሳሰሉ ሊቃውንትና በላይን በመሳሰሉ ጀግኖች የመንፈስና የሞራል ልእልና ነው። ይህን በትኩረት የተመለከቱ Iris  Habib el Masri የተባሉትና የመሳሰሉ  ጸሀፊዎችም፦

**the sheep of Ethiopia have been delivered from the hyenas of the west by the docrines of st. Mark and the Apostle an saint Cyril**¡ እያሉ በመጽሐፋቸው የገለጹት ከዚህ በመነሳት ነው።

እኒህ አርበኛ፣ ምሁርና ቅዱስ አባት ሊቀጠበብት አድማሱ  በዘመነ ወረራ ለአገራችንና ለቅድስት ቤተክርስትያናችን ያበረከቱትን  አስተዋፆ

**ጨልፌ አቀርብኩላችሁ፤ ድህረ ወረራ ያበረከቱትንም ቀጥየ በማቀርብላችሁ ጊዜ እስክንገናኝ ደህና ቆዩልኝ።**

***የመጀመርያው ክፍል፡-የመላከ ብርሀን አድማሱ ጀምበሬና የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ አጽም ፍልሰት***

**http://www.mereja.com/amharic/542371 ወይም http://amharic.abbaymedia.com/archives/33517**

***ሁለተኛው ክፍል፡-አጽማቸው የፈለሰው መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ማናቸው?***

**79344**